

# የኩራት ጽምፅ



ሰኔ 2017
ቅፅ ፫ | ቁጥር ፩

ኒስኒስ ትኩረቷን በLBQ ላይ አድርጋ በየሩብ ዓመቱ በኩዌር ኢትዮጵያ የምትታተም መጽሔት

Nisnis – A quarterly magazine published by Queer Ethiopia focusing on LBQ issues

# QUEER ETHIOPIA
# ኩዊር ኢትዮጵያ

«ኩዊር ኢትዮጵያ» የተለያዩ ፆታዊና ወሲባዊ ዝንባሌ ላላቸው ኢትዮጵያዊ ኩዊር ሴቶች እንዲሆን ታስቦ በኩዊር ሴቶች የተመሠረተ አማራጭ ምትዳር ነው ። ይኽውም ሌዝቢያን ፣ ባይሴክሽዋል ወይም ኤሴክሽዋል የሆኑ ሴቶችንንና ትራንስ ሴቶችን ያካትታል ። ይህ ምትዳር የኩዊር ማኅበረሰብ ታሪክ እና የሕይዎት ልምድ ትልቅ ሥፍራ የሚይዝበት ነው ። እንደ ኩዊር ማኅበረሰብ የዕለት ተዕለት ሕይወታችንን ገጠመኞች ፤ የተለያዩ ሰዎችን የግል ታሪኮች ፤ ቃለ- መጠይቆች እንዲሁም ሥነ-ጥበባትን እንደምናካትት ተስፋ እናደርጋለን ። ከነዚህ በተጨማሪም በኢትዮጵያ ውስጥ እና በዲያስፖራ ለሚገኙ ኢትዮጵያውያን ቤተሰቦች ራሳቸውን ሆነው የሚመጡበት የበይነ-መረብ ማኅበረሰብ መድረክ ሆኖ እንዲያገለግል ማስቻል ፍላጎታችን ብቻ ሣይሆን ጥረታችንም ጭምር ነው ።

queerethiopia.com

ethioqueer

QueerEthiopia

etqueerfamily@gmail.com

t.me/queeret


እኩል!
ኳስኳስ |ሰኔ 2017 | ቅፅ ፩ | ቁጥር ፪

# ማውጫ


የአርታዒያን መልዕክት 3

መግቢያ 4–5

አፍሮዳይት 6–7

ብርታት 8–9

ለውጥ 10–13

ጆይ ጆዬ 14–15

ሙብት 16–19

አቢጌል 20–21

የአእምሮ ጤና 22–25

ሉዋም 26–27

ተስፋ 28–31

ጁንግል ጁሊያ 32–33

ፈገግታ 34–35

ከጭንቀት ነፃ 36–37

ኩራት 38–41

ትግል 42–43

# የአርታዒያን መልዕክት

እንኳን ወደ16ኛው የንስንስ እትም በሰላም መጣችሁ!

በዚህ እትም በማህበረሰባችን ውስጥ የሚገኙ በኢንተርኔት እና በአካል ህይወታቸውን አደጋ ላይ ጥለው

ለመብታችን የሚታገሉ አክቲቪስቶችን ይዘን ቀርበናል፡ ፡ ለተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪዎች ትልቅ ጥላቻ ባለባት ኢትዮጵያ የማህበረሰቡ አባል መሆን ብቻውን አደገኛ ነው፡ ፡ ለመብታችን መታገልን መምረጥ ደግሞ የእነዚህን ታጋዮች ህይወት በይበልጥ ችግር ውስጥ የሚከት ነው፡ ፡

ለምን በዚህ ስራ ውስጥ እንዳለች የጠየቅናት ሉዋም መልሷ “ህይወታችን ሁሌም አደጋ ላይ ነው ፤ መረዳዳታችን ለመዳን ነው” ስትል መልሳልናለች፡ ፡ ሉዋም በዚህ እትም ካቀረብናቸው አምስት ጀግና ታጋዮች አንዷ ናት፡ ፡

የኩዊር ንቅናቄ በተለያየ መልኩ ሊገለጽ ይችላል፡ ፡ አንዳንዶች በሶሻል ሚዲያ የተሳሳቱ አመለካከቶችን በመቃወም ፤ የጥላቻ ይዘትን ሪፖርት በማድረግ እንዲሁም እርዳታ የሚያስፈልጋቸው ኩዊሮችን በማገዝ የበኩላቸውን ያደርጋሉ፡ ፡ በሌላ በኩል በአካል በጋራ መጽሀፍ ማንበብ አይነት ዝግጅቶችን በማዘጋጀት ኩዊሮች በነጻነት የሚገኙበትን ቦታ ያመቻቻሉ፡ ፡

ለታጋይ „ጆይ ጆዬ ምክንያቷ ውስጣዊ ነው፡ ፡ “ለነበርኳት የድሮዋ እኔ እና በዚህ ጨለማ ራሳቸውን„እየፈለጉ ላሉ ኩዊሮች የገባሁት ቃል ነው” ትለናለች፡ ፡

በነዚህ ታጋዮች የሚከፈለው መስዋእትነት ወደነጻነት ያመራናል፡ ፡ የወደፊቱ ትውልድ ኢትዮጵያውያን ኩዊሮች የሚያወሷቸው እና በሀገራችን ተቀባይነት ለማግኘት መንገድን የሚጠርጉ ናቸው፡ ፡ ለውጥ ምንም ያህል አስፈሪ ቢሆንም ሊገኝ የሚችለው ራሳቸውን ለዚህ ንቅናቄ የሰጡ ሰዎች የለውጡ ማሳያ ሲሆኑ ነው፡ ፡

ይህ ንቅናቄ እንደ ፐራይድ ፓሬድ እና የቀስተደመና ባንዲራን ማውለብለብ በአደባባይ በሚገለጹ ድርጊቶች የተወሰነ አይደለም፡ ፡ በጸጥታ እና በጽናት የሚደረጉ የኦንላይን ጥላቻን መዋጋት ፤ ራሳቸውን መቀበል ለከበዳቸው ሌሎች ኩዊሮች አለሁላችሁ ማለት በቀስታ ቢሆንም ወደለውጥ የሚመሩ አስፈላጊ የንቅናቄው ገጽታዎች ናቸው፡ ፡

ይሁንና ይህ ስራ በአእምሮ ጤና ላይ የሚያደርሰውን ጫና መካድ አይቻልም፡ ፡ ታጋዮቻችን ራሳቸውን እንዴት እንደሚጠብቁ አጫውተውናል፡ ፡ ታጋይ አፍሮዳይ “በሁሉም ነገር ውስጥ ውበትን ፈልጎ በማግኘት ባለን ነገር አመስጋኝ እንድንሆን ማድረግ ይኖርብናል” ትላለች፡ ፡

ሁላችንም በየራሳችን መንገድ ታጋዮች ነን፡ ፡ ራሳችንን መቀበል ትግል ነው፡ ፡ ከሌሎች ኩዊሮች ጋር መገናኘት ትግል ነው፡ ፡ እውነታችንን መኖር ትግል ነው፡ ፡

በመጨረሻም ይህ የሰኔ ወር እትማችን ዘግይቶ በመድረሱ ይቅርታ እንጠይቃለን፡ ፡ ይህ የንስንስ እትም እንደሚያበረታችሁ እና እነዚህን ጀግና ታጋዮች የሚያከብር እንደሆነ ተስፋ እናደርጋለን፡ ፡

# መግቢያ

በተለምዶ ፐሯይድን ስናስብ የሚታሰበን ሰልፍ ፤ ቀስተደመና ፤ ብዙዎች ተሰብሰበው ከብሩክ ሰማይ ስር ሲደንሱ ነው ፡ ፡ በለሊት ስልክ ላይ የአብሮነት መልእክት የሚጽፍ ብቸኛ ሰውን አናስብም ፡ ፡

በተለምዶ ኀቅናቄን ስናስብ የሚታየን የቲክቶክ ቪዲዮዎች ናቸው ፡ ፡ በሹክሹክታ የሚነገር “አለሁልሽ” ፤ ታሪክ ፤ ወይም እምቢታን አናስብም ፡ ፡

እንረሳለን ፡ ፡

ጀንግል ጁሊያ ሯሳቸውን መሆን አብዮት እስኪሆን ድረስ እውነታቸውን እየኖሩ

ጆይ ጆዬ ወንዳንድ መገለጫን እና አልሰበር ባይነቷን ይዛ ለሰአታት ኦንላይን በመሆን

ለማታውቃቸው ሰዎች “ብቻቸሁን አይደላቸሁም ፤ አለሁላቸሁ” እያለች

አፍሮዳይት ጽናትን እያሳየች በየቀኑ በሚያጋጥመን ጥላቻ ውስጥ እንኳን ሯሳችንን እንድንወድ እያስታወሰችን

አቢጌል የሁላችንን እውነት እውን ለማድረግ ስትል ህይወቷን አደጋ ላ ጥላ የአእምሮ ጤና ታሪኮችን እያጋሯች

ሉዋም ኩዊር ቤተሰቦቻችን ያለፍርሀት የሚተነፍሱበትንና በአካል የሚገናኙበትን ቦታ እያዘጋጀች

በፀጥታ እንድንኖር በሚያስገድደን ሀገር ውስጥ እነዚህ ታጋዮች በድንጋይ ውስጥ የሚበቅሉ አበቦች ናቸው

ብርሀን በማይደርስበት ቦታ እያበቡ

ጥላቻን እየተዋጉ

ተደብቀን አንኖርም እያሉ

ብርታታችን በእነዚህ ጥቃቅን በሚመስሉ አይበገሬ ድርጊቶች ውስጥ እንደሆነ ያስታውሱናል በመገኘት

አለሁ በማለት

እና ሯሳችንን በመሆን ውስጥ

ከዛ በላይ ምን ሀይል አለ

ይህ ለእነሱ ያቀረብነው የአክብሮታችን መገለጫ ነው ፡ ፡


GAY PRIDE
SILENCE=DEATH
IF GOD HATES GAYS WHY ARE WE SO CUTE



# ነቡራት ካብአፍሮዳይት ጋር

አፍሮዳይት ኩዊር
ኢትዮጵያዊ ጸሀፊ ፣
ገጣሚ እና ታጋይ
ስትሆን የሚያበረቱና
ሥስን ስለመውደድ
የሚሰብኩ ግጥሞችና
ታሪኮችን ትጽፋለች ፡ ፡
የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪ
ማህበረሰቡን በስነጽሁፍ
መደገፏን ቀጥላለች ፡ ፡

“ሁላችንም የተፈጠርነው እኩል ሆነን ነው ብዬ አምናለሁ፡፡ ሁሉም ሰው ማንም ቢሆን ፣ ማንንም ቢያፈቅር ተከብሮ የመኖር መብት አለው፡፡ መታየት እና ትምህርት ትልቅ መሳሪያዎች ናቸው ብዬ አስባለሁ፡፡ ብዙ ሰዎች ባዩን እና ታሪካችን በተረዱን ቁጥር ልባቸው እና ሀሳባቸው ይቀየራል፡፡ ይህ ነው የሚያበረታኝ፡፡” – ጀንግል ጁሊያ

“ከሁለት አመት በፊት የጥላቻ ዘመቻ ሲከፈትብን ምን ያህል ፈርተን እንደነበር አስታውሳለሁ፡፡ እንደኩዊር ሳይሆን እንደአክቲቪስት ልንጠቃ እንደምንችል አውቄ ነበር፡፡ ግን በፍርሀቱ ውስጥ አጋሬ ጠንካራ ሆና አገኘኋት፡፡ ድጋፍ ስታሰባስብ ፣ በእንቅልፍ አልባ ለሊቶች ስለጥቃቶች መረጃ ስታጠናቅር ፣ እንዲሁም በጥላቻው ምክንያት ለተሰበሩ ድጋፍ ስትሆን አየሁ፡፡ በዛ ሁሉ አደጋ ውስጥ እንዴት እንዳልተደናገጠች እና ምን እንዳበረታት ስጠይቃት “የማደርገው ሌሎች ለእኔ ያደርጉልኝል ብዬ ተስፋ የማደርገውን ነው አለችኝ” ለዛ ነው እኔም የማላቆመው፡፡ ህይወታችን ሁሌም አደጋ ላይ ነው ስለዚህ ንቁ መሆናችን ለደህንነታችን አስፈላጊ ነው፡፡ ” – ሉዋም

# 1.ካለው አደጋ አንጻር ይህን ስራ እንድትቀጥይ የሚያበረታሽ ምንድነው?

“መጀመሪያ ሩሴን እንደሌዝቢያን ሴት ስቀበል ኢትዮጵያ ውስጥ እንደመሆኑ ብቸኝነት ተሰምቶኝ ነበር፡ ፡ የሚታወቅ ሰው አልነበረም ፤ እንኳ ብቻ አይደለሽም ብሎ የሚነግረኝም ሰው የለም፡ ፡ በኋላ ግን ኦንላይን ከማህበረሰቡ ጋር ተዋወኩ ቀስበቀስ በአካልም ተገናኘን፡ ፡ የኔ የምለው ማህበረሰብ እንዳለኝ ማወቄ የሰጠኝ ሰላም ሁሉንም ነገር ቀየረው፡ ፡ አደጋ ቢኖርም ተስፋ እንዳልቆርጥ የሚያደርገኝ ያ ነው፡ ፡ ያንን ብቸኝነት አስታውሰዋለሁ፡ ፡ ቀጣዩ ትውልድ ያለአጋዥ እንዲኖሩ አልፈቅድም፡ ፡ የምትታይ የምትታወቅ እና “ብቻችሁን አይደላችሁም ፤ አለንላችሁ ፤ ምንም አትሆንም” የምትል ድምጽ መሆን እፈልጋለሁ፡ ፡ ያኔ ብቸኛ ለነበሩኝቸዋ እኔ እና በጨለማ ሩሳቸው እየፈለጉ ላሉ ኩዊር ወጣቶች የምገባው ቃል ነው፡ ፡ ” – ጆይ ጆዬ

“ሂወቴ ስለሆነ በቃ ይህንን ማንነቴን መተው ማለት የሂወቴን ትልቁን ነገር መተው ነው ፡ ፡ አልዋሸሽም አንዳንዴ ሴክሺዋሊቴዬን ዘግይቶ ባውቀው ብዬ ተመኝቼ አውቃለሁ ግን ሂወቴ ነው ! ማንነቴ ነው ! መቼም ልተወው ወይ ልቀይረው አልችልም ፡ ፡ ለኔ ከተሰመረልኝ መስመር ይልቅ ለኔ እውነት የሆነውን መንገድ መምረጥ በእምቢ ባይነት ለመኖር መምረጥ ትልቁ ድሌ ነው ! ነገሮች ከባድ በሆኑበት ግዜ ሁኡ በሩሴ ስኳተምት በሩሴ ከበሮ ልክ መደነስ እወዳለሁ፡ ፡ ” – አቢጌል

“ብቻዬን እንዳልሆንኩ ማወቄ ፤ የእኛ መኖር ለመታገል ብቻ አይደለም ፤ ህይወትን በተወለድንበት መልኩ እንድንኖሩት ነው፡ ፡ በህመማችን ውስጥ እንኳን የምንጋሩው ሳቃችን ይበልጥ ሩሴን እንድሆን ያበረታኛል ፤ ምናልባት አንድቀን ሌሎቹም ይህንኑ እንዲያደርጉ የሚያስችል ቦታ እፈጥሩለሁ፡ ፡ በእኛግጥ አሁንም በትንሹ እያደረኩት ነው፡ ፡ ”
– አፍሮዳይት

# 2.ኢትዮጵያውያን የተመሳሳይ ጾታ አፍቃ
# ማህበረሰቡ አባላትን የሚያዩበት መንገ

“ኢትዮጵያ ውስጥ ብዙ ችግሮች ቢኖሩም ለውጦች አያለሁ። ኩዌር ኢትዮጵያውያን እርስበርስ እየተደጋገፉ እና በፅናት እያደጉ ነው። ከጥቂት አመታት በፊት መተፋፈር፣ ፍርሀት እና ከማህበረሰቡ ራስን ማራቅ የተለመደ ነበር። አሁን ግን እድሜ በግልጽ እንዲሁም በድብቅ ለሚታዩ ኢትዮጵያውያ ጀግና ኩዌሮች፣ ብዙ ሰዎች “እኔም እኮ እንደዛ ነኝ፣ ስህተት አይደለሁም፣ ራሴን ነኝ” ማለት ጀምረዋል። ይህ እውቅና በሹክሹክታም ቢሆን ትልቅ መስታወት ነው። ራስን መቀበል እና አብሮነትን ያሳድጋል። የብቸኝነት ግድግዳ ፈርሶ አሁን በኩራት እና በመፈካለግ እየተተካ ነው። የመረጥነው ቤተሰብ እየመሰረትን፣ ተስፋ እያጋራን፣ እና የጽናት ታሪክን እየጻፍን ነው፡ ይህ ማለት ለወደፊቱ ትውልድ ጉዟቸው ከብቸኝነት የራቀ እና ብዙም አስፈሪ ያልሆነ ይሆናል ማለት ነው። ከብቸኛ” ሰዎች ተነስተን ጠንካራ ራሳችንን የሚያውቅ ማህበረሰብን መስርተናል።
– ጆይ ጆዬ

# ...ዎች ላይ ራሳቸውንም ሆነ ሌሎች የኩዌር
# ...ኛ ላይ ያየኸው አዎንታዊ ለውጥ አለ?

“ትልቅ ለውጥ ኢትዮጵያውያ ኩዌሮች የኩም የሚለውን ውሸት መግፈፋችን ነው ፡ ፡ ከአስር ወይም አስራምስት አመት በፊት ሀጥያተኛ አይደሉም ፤ የተረገሙ አይደሉም ብሎ የማይለን ሰው አይገኝም ነበር ፡ ፡ ዛሬ ላይ ግን እንደተጠቂ ወይም ሀጥያተኛ ሳይሆን ክብርን እንደሚፈልጉ የሰው ልጅ የሚያዩን ሰዎች አሉ ፡ ፡ ይህ ለውጥ የመጣው ኩዌሮች ራሳቸውን ለአደጋ አጋልጠው በመውጣታቸው ነው ፡ ፡ አዎ መታየት ከ“ጥቃት ያጋልጠናል ግ”ን በግልጽ ያልወጣ ኩዌር ሰው ይህን ቃለመጠይቅ ሲያነብ “ለካ አልተሰበርኩም” ብሎ ያስባል ፡ ፡ ይህ የጸጥታ አብዮት ነው ፡ ፡ ኢትዮጵያ ውስጥ እስር እና የአድማ ጥቃት ባለበት ሁኔታ ለራሳችን ያለንን ዋጋ ማወቅ ጦርነት ነው ፡ ፡ ግን ለውጥ የምንለው ትልቅ ዝግጅቶች እና ባንዲራችንን ማውለብለብ ሳይሆን ልባችን እንደተጠበቀ መዳናችንን ነው ፡ ፡ በማህበረሰባችን ውስጥ ፀጥተኛ አብ”ዩት አቀጣጥለናል ፡ ፡ አሁን ጠንካራ እና ከበፊቱ ባነሰ በራሱ የማያፍር ሆኗል፡፡ ” – ሉዋም

“አሁንም ብዙ ጉዞ ይቀረናል ግን ብዙ ኩዊር ኢትዮጵያውያን ሎሳቸው ይበልጥ እየሆኑ እንደሆነ ተመልክቻለሁ ፡ ፡ የተሻለ በሎስ መተማመን እና ያለይቅርታ ማንነታቸውን በትንንሽ መንገዶችም ቢሆን መቀበልን እያየሁ ነው ፡ ፡ ተስፋ” ይሰጠኛል ፡ ፡

– ጀንግል ጁሊያ

“እዚህ በነበርኩበት አጭር ጊዜ ውስጥ መልካም አዕምሮ ያላቸው ወጣቶች ማህበረሰቡን በሚያስተሳስር እና አንድነት በሚፈጥር መልኩ ሎሳቸውን ሲገልጹ ተመልክቻለሁ ፡ ፡ በጣም ወድጄሻለሁ ፡ ፡ የተወሰኑትን ለመጥቀስ ፍሬን ቤኪ ፤ ሮቢን እዮአብ ፤ ሲፈን ፤ እና ጋብሬኤላ ጀግኖች እና ውብ ማንነት ያላቸው ወጣቶች ናቸው ፡ ፡ እንደነሱ ካሉ ሌሎች ሰዎችም ተጨማሪ ፓስቶች ባይ ደስ ይለኛል ፤ እንዲሁም ካለ አላውቅም ግን ሰዎች የእለት ተእለት ውሏቸውን የሚያጋሩበት የ”ግሩፕ ገጽ ቢኖር መልካም ነው ፡ ፡

– አፍሮዳይት

“እኔ Sifen, below Freen Becky ,Robin ,Gabriela የመሳሰሉ በጣም ጎበዝ ልጆች ስለ ኮሚኒቲ ፣ ስለ transgender inclusion ፡ ስለ አክቲቪዚም እንዲሁም ስለ ጄግንነት የነበረኝን አመለካከት ቀይረውታል ። እነዚህ ውይይቶች ደግሞ የአመለካከት ለውጥ የሚያመጡ ናቸው ። ! በብዙ መንገድም መጻፍ እንድቀጥል inspire ያደርጉኝ ልጆች ናቸው ፡ ፡ በጣም ብዙ ኢነርጂያቸው እሚጋባብኝ ልጆች አሉ ፡ ፡ አንዴ ታሪክ መጻፍ ስጀምር ብውስጥ መጥቶ የሚያወሯኝ ሰው ብዙ ነው ፡ ፡ በርቺ የሚለኝ ሰው ይበዛል ! ኮመንት ላይ መጻፍ አንችልም የሚሉኝ ብዙ ሰዎች ናቸው ። ብዙ ሰዎች ያወሩኛል ይሄን ሳይ ትንሽም ቢሆን ለውጥ እያመጣሁ እንደሆነ ይሰማኛል !! ስለኛ ኮሚኒቲ ፣ ስለ አካታችነት ፣ ስለ ወዳጅነት እንዲሁም አለማቀፍ ስለሆነው queer movement ብዙ ተምርያለሁ ፡ ፡ ስለሁሴም ብዙ ነገር እንድማር ፡ና ሳላውቀው የተቀሃደኝን ልክ ያልሆነ አስተሳሰብ እንድረዳ አድርጎኛል ፡ ፡

– አቢጌል

ጆይ ጆዬ ወንዳወንድ ሌዚቢያን ስትሆን የኢትዮጵያን ኲዊር ማህበረሰብ በኦንላይን እና አካል ንቅናቄ ለማበርታት ትሰራለች፡፡ ስራዋ ለኲዊር ሰዎች መድረክን መፍጠር እና የኦንላይን ደህንነታቸው የተጠበቀ መሆኑን ማረጋገጥ ያካትታል፡፡

# ኩራት ከጆይ ጆዬ ጋር



# ፫. በኢትዮጵያ ለሚገኙ የተመሳሳይ ጾ
# አለቸኳቧይ ህጋዊ ወይም ማህ

# ጾታ አፍቃሪዎቹ በጣም አስፈላጊ እና
# ህበረሰባዊ ለውጥ መንጃነው?

“ከህግ አንጻር ምንም አልተቀየረም አሁንም እንደወንጀለኛ ነው የምንታየው ፤ ይህ ደግሞ በምናደርገው ነገር ውስጥ ሁሉ የምናስበው ነው፡፡ እንደማህበረሰብ ግን ትንሽም ቢሆን ለውጥ አለ፡፡ ይቀበሉናል አልልም” ግን አንዳንዱ ሰዎች “አያገባኝም” አይነት አመለካከት እያዳበሩ ነው፡፡ እንደማሸነፍ የሚወሰድ ነገር አይደለም ግን በእኛ ሁኔታ ሲታሰብ ቢያንስ ጥቃትን ስለማያበረታታ ጥሩ ለውጥ ነው፡፡”

– ጆይ ጆዬ

“እውነት ለመናገር አሁን ላይ ይህ ነው የሚባል ለውጥ አለ ብዬ አላስብም ግን ጉዞአችን ይቆማል ማለት አይደለም፡፡ ለውጥ ኑቅ ቢመስልም ትግላችን ይቀጥላል፡፡”

– ጂንግል ጁሊያ

“እውነት ለመናገር ህጉን ከመቀየር ይልቅ ልቦችን ስለመቀየር አልማለሁ፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ የምትገኝ የተቃራኒ ፆታ አፍቃሪ ለእኩል ደሞዝ የምትታገለውን ያህል ለእኔም መብት እንድትታገል እፈልጋለሁ፡፡ የእኔና የእሷ ነጻነት የተያያዘ እንደሆነ ሁላችንም የምንሊዳባትን ሀገር እናፍቃለሁ፡፡ የተለመደ ጥቅስ ቢመስልም ሁላችንም ነጻ ካልሆንን ማናችንም ነጻ አይደለንም፡፡ ህግ ጊዜ ይወስዳል አስተሳሰብን መቀየር ግን አስቸኳይ እና በጣም አስፈላጊ ነው፡፡”


– ሉዋም

“የአእምሮ ጤንነት እና አብሮነታቸውን ላይ በደንብ መስራት ይኖርብናል ፡ ፡ በትንንሽ ነገሮች ሰዎች ተከፋፍለው ማየት በጣም ያሳዝናል ፡ ፡ እንዲሁም ከሰፊው ማህበረሰብ ተገለን እየኖርን ነው ፤ ይህን የሚያባብስ ተጨማሪ መከፋፈል በመሀላችን ለምን እንደምንፈጥር አላውቅም ፡ ፡ ”

– አፍሮዳይት

“እዚህ ሀገር ካሉ ሁሉም የማህበራዊ መስተጋብሮች መገለል ደርሶብናል ራሳችንን መስለን መኖር ይቅር እና ማንነታችን ሲጠርጠር ህወታችን አደጋ ላይ ነው ! በዚያ ላይ ጋብ ያለ ሲመስል መልሶ የሚነሳው የ hate campaign አለ! በመሀላችን ሌላ የሚያዳክም ነገር ለምን እንደምንፈልግ እና ከመደጋገፍ መጠላለፍ እንደምንፈልግ አይገባኝም! እዚያው ኮሚኒቲያችን ውስጥ የምትሰሚው ብዙ ስድድብ ፣ ደስ የማይል ገጠመኝ እና አሳዛኝ ታሪክ አለ ! ለኔ የሚታየኝ በመካከላችን ያሉት ችግሮች ላይ መስራት ነው፡፡ ”

– አቢጌል



# ኑራት ከአቢጌል ጋር

አቢጌል ኢትዮጵያዊት ኡዋር ስትሆን የአእምሮ እና ወሲባዊ ጤና ላይ አተኩራ ትሰራለች ፡ ፡ በፌስቡክ በምታጋራቸው የግል ታሪኮቿ ሌሎቹም ራሳቸው እንዲቀበሉ እና እንዲወዱ ማድረግ እንደምትችል ተስፋ ታደርጋለች ፡ ፡

“ኢትዮጵያ ውስጥ ካለው ሁኔታ አንጻር የአእምሮ ጤናን መጠበቅ ከባድ ግን አስፈላጊ ነው ፡ ፡ በተቻለ መጠን ተስፋ እና ለውጥ ላይ ትኩረት በማድረግ ትንንሾቹንም ስኬቶቼን አከብራለሁ ፡ ፡ ያሉኝ ኩዊር የቅርብ ጓደኞቼን እና የመረጥኳቸው ቤተሰቦቼ ህይወቴ ማለት ናቸው ፤ ሁሉንም ነገር እንጋራለን ፤ በቀልዶቻችን ውስጥ ጥንካሬን እናገኛለን ፤ ይህ ደግሞ ለህመማችን ጥሩ መድሀኒት ነው ፡ ፡ ከምንም በላይ ግን አዳዲስ ፊቶችን ሳይ እና ደህንነት ሲሰማኝ የመረጋጋት ስሜት ይሰጠኛል ፤ ለምን እንደምፋለምም ያስታውሰኛ፡ ፡ ብርታት የሚሆነኝ እና አላማዬን የሚያስታውሰኝም ያ ነው ፡ ፡

– ጁይ ጁዬ

# 4. በዚህ ስራ ውስጥ የአእምሮ ጤናዎን በምን መልኩ ይጠብቃሉ?

“የአእምሮ ጤናዬን የምጠብቀው ራሴን በመልካም ሰዎች በመክበብ ነው። የስጋ ቤተሰቦች እና የመረጥኳቸው ቤተሰቦቼ አሉ። የውጪው አለም ከባድ ሲሆንብኝ ወደራሴ ጥንካሬ እና የቅርቤ ወደምላቸው ሰዎች እዞራለሁ። አነባለሁ። ጥሩ ሙዚቃ አዳምጣለሁ። ምግብ እና ቆንጆ ውይይቶችን እጋራለሁ። ሰውነቴን አንቀሳቅሳለሁ። እንዲሁም ወደአጋሬ እሄዳለሁ እሷም አቅዳ ብቻዬን እንዳልሆንኩ ታስታውሰኛለች። በእቅፏ ውስጥ ይሄ ትግል ለምን እንደሚያስፈልገን አስታውሳለሁ። – ሉዋም

“ለራሴ ቦታ መስጠትን ተምሬያለሁ ፡ ፡ በምችል ሰአት ሜዲቴት አደርጋለሁ ፡ ፡ ሆኖ ብዬ ከራሴ ጋር ጊዜ አሳልፋለሁ ፡ ፡ ሙዚቃ በጣም ይረዳኛል ለእኔ እንደቴራፒ ነው ፡ ፡ ከምንም በላይ ደግሞ ሁሌም ከፍ የሚያደርጉኝ እና የሚያቃኑኝ ጓደኞች አሉኝ ፡ ፡ ፍቅራቸው እና መኖራቸው ሰላም ይሰጠኛል ፡ ፡”

– ጀንግል ጁሊያ

“ደህነቴ ላይ በጣም ጠንቃቃ ነኝ ራሴን ላለማጋለጥ በጣም እጠነቀቃለሁ ሁሉም ማህበራዊ ድረገጾች ላይ anonymous ነኝ ፧ ነገሮች በጣም መካረር ሲጀምሩ እና የጥላቻ ካምፔይኖች መካረር ሲጀምሩ ድህነቴንም የአእምሮ ጤናዬንም ለመጠበቅ ራሴን አገላለሁ! ተሳትፎዬ በጣም ይቆጠባል ፡ ፡”

– አቢጌል

“አንድ ሴት ሌላ ሴት ማፍቀርን ሳንጨምርበት ሁሉ ህይወት እንደሆነ ከባድ እንደሆነ ይገባኛል ፤ ግን ሁስሽን አይተሻታል? አንቺን ማን ላይወድሽ ይችላል? እንደእኔ ሴትነትሽ እና ውበትሽ አደገኛ መስሎ እንዲሰማሽ ያደረገሽ አለም ላይ ካደግሽ ደግሞ ኩዊር መሆን ከፍቅርም በላይ ነው ፡ ፡ ሌላ ሴትን በእውነተኛ ስሜት ማፍቀር የሁስሽን ነጸብሁቅ ማየት ፤ ማየት እና መታየት ማለት ነው ፡ ፡ መስታወትሽ ትሆናለች ፤ በሁሉ ነገር ልክ ባትሆንም ፤ ነጻ ፤ ጠንካሁ እና የማትገበር ናት ፡ ፡ ኪዊር ሴቶችን ማየት የጀመርኩት ስለሁሴ እንደተማርኩ ነው ይህን ስል በጾታዊ ዝንባሌ ብቻ ሳይሆን እንደጠንካሁ እና ከማህበረሰቡ ክልከላ ወጥታ የሁሷን እውነት እና ብርሀን እንደምትፈልግ ሴት ማለቴ ነው ፡ ፡ ማንም ብትሆኚ እኔን ስለሆንሽ እወድሻለሁ ፡ ፡ ” – አፍሮዳይት

ሉዋም ህይወቷን
ለተመሳሳይ ጾታ
አፍቃሪዎች መብት
ንቅናቄ አሳልፋ የሰጠች
ኢትዮጵያዊ ኲዊር
ናት ፡ ፡ ለኲዊር ሴቶች
ደህንነታቸው የተጠበቁ
ቦታዎችን ከመፍጠር
በተጨማሪ በኢትዮጵያ
የሚገኘውን ማህበረሰብ
ልምድ በማጠናቀር
በመረጃነት ትይዛለች ፡ ፡

# ኩራት ከሉዋም ጋር



# ፭.በብቸኝነት እና ተስፋ መቁረጥ ውስጥ ያ
# ይፈል

“አንድ ሴት ሌላ ሴት ማፍቀርን ሳንጨምርበት ሁሉ ህይወት እንደሆነ ከባድ እንደሆነ ይገባኛል ፤ ግን ሁስሽን አይተሻታል? አንቺን ማን ላይወድሽ ይችላል? እንደእኔ ሴትነትሽ እና ውበትሽ አደገኛ መስሎ እንዲሰማሽ ያደረገሽ አለም ላይ ካደግሽ ደግሞ ኩዊር መሆን ከፍቅርም በላይ ነው ፡ ፡ ሌላ ሴትን በእውነተኛ ስሜት ማፍቀር የሁስሽን ነጸብሁቅ ማየት ፤ ማየት እና መታየት ማለት ነው ፡ ፡ መስታወትሽ ትሆናለች ፤ በሁሉ ነገር ልክ ባትሆንም ፤ ነጻ ፤ ጠንካሁ እና የማትገበር ናት ፡ ፡ ኪዊር ሴቶችን ማየት የጀመርኩት ስለሁሴ እንደተማርኩ ነው ይህን ስል በጾታዊ ዝንባሌ ብቻ ሳይሆን እንደጠንካሁ እና ከማህበረሰቡ ክልከላ ወጥታ የሁሷን እውነት እና ብርሀን እንደምትፈልግ ሴት ማለቴ ነው ፡ ፡ ማንም ብትሆኚ እኔን ስለሆንሽ እወድሻለሁ ፡ ፡ ” – አፍሮዳይት

# ...ሉ የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪያን መን ማለት ...ፖሉ ?

“ሃሳቸውን እንዲቀበሉ ማድረግ ብችል ደስ ይለኛል ! ሃሳችንን የተቀበልነው የኮሚኒቲው አባላት ምርጥ ምንጣፍ መሆን መቻል አለብን ብዬ አስባለሁ ! ሃስን መቀበል ቀላል ጉዞ አይደለም ነገር ግን ሃሳቸውን መቀበል እንዳለባቸው ነው መናገር የምፈልገው ። ይህን አድካሚ መንገድ የመጣ ሰው ኮሚኒቲያችን መሀል ያሉ ችግሮች እንዳያስደነብሩዋቸው marginalized community የሚያልፈበት ፈታኝ ጉዞ መሆኑን ቢረዱት ብዬ አስባለሁ ።

– አቢጌል

“ አንደኛ ብቸኛ አይደላችሁም ፡ ፡ ብዙዎቻችን በእናንተ ቦታ ነበርን ፤ እንደማንታይ ተሰምቶን ተሰብረን እናውቃለን ነገሮች ግን ቀስበቀስ ቢሆንም ሁሌም የተሻለ ይሆናሉ ፡ ፡ መልካም እና ከሚረዱ ሰዎች ጋር አስተዋውቃቸዋለሁ ፡ ፡ ደስታን ማግኘት ፤ መሳቅ ፤ መደነስ ከጥንቃቄ ጋር እንደሚቻል አስታውሳቸዋለሁ ፡ ፡ ከምንም በላይ ደግሞ “ማንነታችሁ ዋጋ አለው ” እላቸዋለሁ ፡ ፡

– ጀንግል ጁሊያ


“የሚያፎን የሚመስለውን የብቸኝነት ስሜት እረዳዋለሁ ፤ ያለማንም ብቻችንን እንደሆንን የሚሰማንን ስሜት ሁላችንም ተሰምቶናል ፡ ፡ ግን እባካችሁ ብቻችሁን እንዳልሆናችሁ አስታውሱ ፤ ያ ስሜት እስከመጨረሻው አብሯችሁ አይቆይም ፡ ፡ ከቻላችሁ ለራሳችሁ ልታደርጉት የሚገባው ነገር ከሌላ ኩዌር ሰው ጋር መገናኘት ነው ፡ ፡ አውቃለሁ አስፈሪ ነው ፤ ግን ማንነታችሁን ሳታሳውቁ ኦንላይን ግሩፖች ውስጥ መሳተፍ ወይም በጣም በጥንቃቄ እና የሚቻል ከሆነ በአካል መገናኘት ይረዳል ፡ ፡ የሚረዳችሁ ሰው እንዳለ ማወቅ እና ለካ ብቻዬን አይደለሁም የሚለውን ስሜት መሰማት ለነፍሳችሁ„እንደቅባት ነው ፡ ፡ ስለእናንተ የሚናገሩ ታሪኮችን አንብቡ” ፖድካስቶች አዳምጡ ፤ የኩዌር ዌብሳይቶችን ተመልከቱ ፤ ቃላቶቻቸው እና ድምጻቸው ጓደኛችሁ እንዲሆን አድርጉ ፤ ከብቸኝነታችሁ ውጪ ሌላ አለም እንዳለ ማስታወሻ ይሁናችሁ ፡ አንድ ሰውም ቢሆን ከምታምኑት ሰው ጋር አውሩ ፡ ፡ ፍ„ታ ከከበዳችሁ ደግሞ እርዳታ ጠይቁ ፤ ሁላችንም አልፈንበታል” ፤ አብረን እንወጣዋለን ፡ ፡

በዚህ ሁሉ ውስጥ ግን ልቤን ቢሰብረውም ተጠንቀቁ ማለት እፈልጋለሁ ፡ ፡ ተቀባይነት ማግኘት ህልም የሆነበት ሀገር ላይ ነን ፤ ለምድ የለበሱ ተኩላዎች አሉ ፤ በድክመታችን ሊያጠቁን ይፈልጋሉ ፡ ፡ ጎበዝ ፤ ጠንቃቃ ሁኑ ፡ ፡ ደህንነታችሁ አስፈላጊ ነው ፡ ፡ ፍቅር ፤ ተቀባይነት ፣ ደስታ ይገባቻኋል ፡ ፡ መኖራችሁ ራሱ የጽናት መገለጫ ነው ፡ ፡ ” –፳ይ ፳ዬ

“ብቸኝነት እና ተስፋ መቁረጥ ለሚሰማችሁ ፣ አንደኛ በጥልቀት ተንፈሱ፡ ፡ ደርሳችኋል፡ ፡ እዚህ ቤተኛ ናችሁ፡ ፡ የትም ብትሆኑ ይህ ቤታችሁ ነው፡ ፡ ከባድ እንደሆነ አቃለሁ ፣ ፍርሃታችሁ ይገባኛል፡ ፡ ብቸኝነት እና ሀዘናችሁ የኔም ነው፡ ፡ ግን ስሙኝ አልተሰበራችሁም ፣ በጭራሽ! እስኪያብብ የሚጠብቅ ዘር ናችሁ፡ ፡ ዝም ያለ ፣ ጠንካራ እና ውብ ማህበረሰብ አላችሁ፡ ፡ ስታለቅሱ አብረናችሁ እናለቅሳለን፡ ፡ ተስፋ ስታደርጉ አብረናችሁ ተስፋ እናደርጋለን፡ ፡ ስትደንሱ አብረናችሁ እንደንሳለን፡ ፡ ወደትንንሾቹ ደስታዎች ፊታችሁን አዙሩ፡ ፡ ትከሻችሁን እስክስ የሚያስብል ሙዚቃ ፣ ቆንጆ ማኪያቶ ፣ በነሃሴ ዝናብ ብቅ የምትል ጸሀይ ፣ እነዚህን በልባችሁ አኑሩ፡ ፡ ደስታ ሁሉም ቦታ እንዳለ ማስታወሻችሁ ይሁኑ፡ ፡ ገና ባላገኛችኋቸው ሰዎች እንደምትወደዱ አስታውሱ፡ ፡ በርቱ ፣ እንወዳችኋለን ፣ የነገዋ ኢትዮጵያ ትፈልጋችኋለች፡ ፡ ” – ሉዋም

# ኩራት ከጆንግል ጁሊያ ጋር

ጀንግል ጁሊያ የጾታ መገለጫ የሌላቸው ኢትዮጵያዊ ሲሆኑ ለማህበራዊ ለውጥ ተግተው ይሰራሉ፡፡ ትምህርት እና እውቅና ወደአዎንታዊ ለውጥ ያመራናል ሲሉ ይናገራሉ፡፡ ትግላቸውን በተለያዩ ዝግጅቶች በመሳተፍ እና ራሳቸውን በመሆን ይገልጹታል፡፡



“ሁሉም ፈገግ የሚያስብለኝ ኩዊር ሰው ሲያጋጥመኝ ወይም የቀን ተቀን ህይወታችን ውስጥ ትኛሽ እና የማያስታውቅ ኩዊርነትን የሚያሳይ ነገር ሳይ ነው። ሁለት ሴቶች ለየት ባለ ስሜት ውስጥ ሆነው ሲለመዱ ሊሆን ይችላል ወይም ያልተጋነነ የኩዊር ቀለማትን የያዘ ጥላን የያዙ በእድሜ ትልቅ ሴት ሳይ ማህረሰባችን ያስታውሰኛል። ትልልቅ ነገሮች መሆን የለባቸውም ትኛሽ ፤ ያለቃላት የምንግባባቸው ማረጋገጫዎች በቂ ናቸው። ለመኖራችን ውብ እና በቂ ማስታወሻ ናቸው።”

– ጆይ ጆዬ

“ድመቶቼ የማይሆን ነገር ሲያደርጉ ማየት ፤ የሌለ ነገር ሲያባሩ ፤ ጥላ ሲያስደነግጣቸው ፤ ቀኑ ምንም ያህል ከባድ ቢሆንም ያስቁኛል።”

– ጀንግል ጁሊያ

“ፀሀይ ፊቴን ስትነካኝ። ኢትዮጵያ ውስጥ ባለው ጥላቻ ምክንያት ወደምእሩቡ አለም መሄድን ሳስብ በክረምት ጨለማ እንዴት እሆናለሁ” ብዬ አስባለሁ። የ13 ወር ጸጋ። ጸሀይ ተአምር ናት።” – ሉዋም

“ከሁሉም አቅጣጫ ነጻነታችንን ለመንጠቅ የሚሞክረውን ሀይል በመታገል ለራሳችን እውነት በሆነ መልኩ የመኖር ጽናታችን እና አይበገሬነታችን። በዚህ ሁሉ ጥላቻ እና በደል ውስጥ መኖራችን ተአምራዊ ነው። አሁንም አለን ፤ በምንችለው መልኩ እንወዳለን ፤ ፍቅራችንን እንገልጻለን ፤ ህይወትን በራሳችን ህግ እንኖራታለን! ”ይሄ ነው! ይሄ ጀግንነት ካልተባለ ምን እንደሚባል አላውቅም።

– አፍሮዳይት

“ብዙ ግዜዬን የማሳልፈው ከራሴ ጋ ነው ! ሙዚቃ በጣም እወዳለሁ ፣ ፊልም ማየት ፡ ረጅም መንገድ መጓዝ ፣ ጸጥ ያሉ ካፌዎች መሄድ ፣ ሃይቅ ዳር ሄጄ ቁጭ ብዬ ማሰብ ያስደስተኛል በተለይ ካፌ ሄጄ ብቻዬን ቁጭ ማለት ያስደስተኛል ፣ ቤተ ክርስትያንም እሄዳለሁ ጸጥታው ዝማሬው ያስደስተኛል ።

– አቢጌል

# 6. አንድ ቀላል በየቀኑ ፈገግ የሚያስብልሽ ነገር ምንድነው?




“የአጋሬን እጅ ይዤ ሙሉ አዲስአበባን በኩራት ያለምንም ፍርሃት እና መጠንቀቅ እራመድባት ነበር ፡ ፡ እንደሁሉም ሰው “ዋክ” አደርጋለሁ ፡ ፡ ”
– ጆይ ጆዬ

“ኢትዮጵያ አይታ የማታውቀውን አይነት ትልቅ የኩዊር ማህበረሰብ ፓርቲ አዘጋጅ ነበር ፡ ፡ ሙሉ ቀን ስንዝናና ፤ ታለንት ሾው ስናቀርብ ፤ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሲሰጥ ፤ አነቃቂ ንግግሮች ሲነገሩ ፤ ስንደንስ እንዲሁም መጋባት ለሚፈልጉ ደግሞ ትናንሽ ሰርጎች የምናዘጋጅበት አይነት ፓርቲ አዘጋጃለሁ ፡ ፡ ደስታ እና ነጻነት ያለበት ቀን ፡ ፡ ህልሜ ነው ፡ ፡ ” – ጀንግል ጁሊያ

“ከሌሎች ሰዎች እና ከተፈጥሮ ጋር እውነተኛ ግንኙነት የሚኖረኝ ”
– አፍሮዳይት

“በጤና ዙርያ STI (sexually transmitted disease ) በ ወሲብ የሚተላለፉ በሽታዎች ዙርያ ያለው ዝቅተኛ ግንዛቤ ያሳስበኛል ። የአእምሮ ጤና ፡ የ አጠቃላይ የወሲባዊ ጤና ግንዛቤ መፍጠር እና ተደራሽነቱ በነጻ እንዲሆን የማደርግ ይመስለኛል ፡ ፡ እኛ ኮሚኒቲ ላይ፣ በጣም ሊሰራበት የሚገባ ነገር ነው ብዬ አስባለሁ ። ” – አቢጌል




“በለሊት ተነስተን እየተቃቀፍን እየሳቅን የሥሳቾችንን ጊዜ እናሳልፋለን፡፡ ከታቾኛው ክፍል እናቷ ለምን አረፈዳችሁ ብለው ሲቆጡን እህቶቻችን ደግሞ ከእኔና ከእሷ ማነው እድለኛ እያሉ ይበሻሽቃሉ፡፡ ሁሉም ሰው በእሳት ዙሪያ ተሰብስቦ እናቷ ቡና እያፈሉልን ነው፡፡ የቡናው እና የእጣኑ ሽታ ቤተሰባችንን ስንቀላቀል ይቀበለናል፡፡ ቀኑን ሙሉ ሳቅና ብርሀን አብሮን ውሎ ለምሽቱ ያዘጋጇናል፡፡

ሲመሽ እጅ ለእጅ ተያይዘን በአበቦች መሀል እንሯሯጣለን፡፡ የሀበሻ ቀሚስ የለበሱ ሴቶች እልል ብለው ይቀበሉናል፡፡ ከሚወዱን መሀል ሆነን ቃል እንገባባለን፡፡

በሚያምረው አዳራሽ ጠረጴዛው በዶሮ ወጥ፤ ክትፎ እና ጥሬ ስጋ ተሞልቷል ግን ትልቁ ድግስ ጭፈራው ነው፡፡ እንደውሃ ነው የምትንቀሳቀው፤ ያለጥርጥር የሚመጣ ውበት፤ ስታምር! አቅፌያት ጣቶቿን እንዳልረግጥ እየተጠነቀቁ እንደንሳለን፡፡ ቀስ ብለን፤ ግንባራችን እየተነካካ በዙሪያችን ያሉት እንግዶቻችን የሚታዩኝ አይኖቿን እስካይ ድረስ ብቻ ነው፤ አይኖቻችን ሲገጣጠሙ ሁሉም ይደበዝዛል፡፡ በኋላ ላይ እናቶቻችን ከበሮ ሲመቱ ምድርን በሚያንቀጠቅጥ ጭፈራችንን ቤቱን እናደምቀዋለን፡፡

ሁለት ሴቶች፡፡ አንድ ሰርግ፡፡ ያለድብብቆሽ፡፡ ቀኑን እንደጀመርነው እንጨርሰዋለን፡፡ ተቃቅፈን፤ በሹክሹክታ ቃል እየተግባባን ከጨጉላ ክፍላችን ጸሀይዋ ስትወጣ እያየናት ይነጋል፡፡ – ሉዋም

# 8. ლექ

# ሰራውታል?

በጽናታችን
እኮራለሁ ፡ ፡ ደክሞነም
ስለምንደነስ ፣
በህመም ውስጥ ተስፋ
ስላለምናደርግ ፣ አለም
ተው እያለነም
ስለምናፈቅር እኮራለሁ ፡
፡ ኩራቴ ስላለመፍራት
አይደለም ፡ ፡ ስስ ፣
ግልጽ ፣ ደረቅ
በመሆን እንደዛም ሆኖ
ስላለመሸነፍ ነው ፡ ፡

– ሉዋም

ለነጻነቴ መታገሌ ፣
ህይወቴን መልሼ
የራሴ ለማድረግ ፣
ማህበረሰቡ ባስቀመጠልኝ
መስፈርት ሳይኖር ነፍሴ
በወደደችው መልኩ
ለመኖር እና ለማኖር
መታገሌ፡ ፡ነገሮች ከባድ
ሆነው ራሱ በራሴ
ሙዚቃ መወዛወዜ
ያኮራኛል፡ ፡

– አፍሮዳይት

ራሴን መሆኔ ፣
ማስኩሊን መገለጫ
ያለኝ ኢትዮጵያዊ ሴት
ሌዝቢያን መሆኔ ፡
፡ ሌሎች ኩዊሮችን
በምችለው አግዛለው ፣
ተደብቀው እንዳይኖሩ
የሚያስችል ወደፊትን
ለመፍጠር እሰራለሁ ፡ ፡
የሚያኮራኝ ይህ ነው ፣
ራሴን መምረጤ ፣ እኛን
መምረጤ ፣ በዚህ ሁሉ
ሁኔታ ውስጥም ራሴን ሆኜ
መኖሬ ያኮራኛል ፡ ፡


– ጆይ ጆዬ

ራሴን መቀበሌ! ራሴን መሆኔ
የኩራቴ ምንጯ ነው 99%
እየተቃወመኝ እኔ ብቻዬን
መቆሜ ቀላል አይደለም ይህ
ያስደስተኛል ፡ ፡ ሌላው በኛ
ኮሚቴ ውስጥ ያለው ጽናት
እምቢ ባይነት ! ልብ ብለሽ
ካየሽው እኮ የኛ ቆሞ መሄድ
መቻል የሆነ ተአምራት ነው
የሚመስለው በዚህ ሁሉ ጥላቻ
እና በደል መሀል እስከአሁን
በፍቅር ተሞልተን ፣ ራሳችንን
ሆነን ፣ ራሳችንን እየገለጽን አለን
፡ ፡ ከዚህ በላይ እምቢተኝነት
እና ኩሩነት ምን አለ ?

– አቢጌል

ነፍስ እና ስጋቸውን ሰጥተው
ለመብታቸው እና የራሳቸውን መንገድ
ለመከተል በተፋለሙት የኩዊር ጀግኖች
እኮራለሁ ፡ ፡ ለሳይንስ እና ጥበብ
አበርክቶት ባደረጉ ያለፉም የአሁኖቹም
ኩዊር ቤተሰቦቼ እኮራለሁ ፡ ፡ እንደ
ተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪ ኢትዮጵያዊ
በየቀኑ ጥላቻ እና ጥቃትን እየተቋቋሙ
በሚኖሩ እህት እና ወንድሞቼ እኮራለሁ ፡
፡ ሁላችንም ለመዳን እየተፍጨረጨርን
ብቻ አይደለም ፡ ፡ አንዳንዶቻችን
በዚህ ሁኔታ ውስጥ ራሱ ስኬታማ ነን ፡
፡ ልዩ በመሆናችን ፤ በብርሃናችን ፤
በማራኪነታችን እና መቼም በማንነጠቀው
አይበገሬነታችን እኮራለሁ ፡ ፡

– ጀንግል ጁሊያ



**Robin Eyoab**
እንዲ ነው የምለው grand ነገር የለም ነገር ግን መብቴ መኖሬን ማረጋገጥ ነው ብዬ አምናለሁ ስለዚህ ጥላቻን ከውስጤ ነቅሶ ማውጣት መርጣለሁ የራሴን ሁለንተና ሙሉ ለሙሉ በመቀበል እና በመውደድ መብቴን አከብራለሁ ለራሴ ብቻ አይደለም ሌሎችም ይህን መረዳት እንዲችሉ ከመናገር አልቆጠብም

ሌላው ለመብቴ ቆምኩ የምለው የጥላቻ ንግግሮችን ደህንነቴን በማይጎዳ መልክ ስቃወም ነው ከቤተሰብ ከጓደኞቼ ወይም ከሌሎችም ዜጎች ጋርም ቢሆን

ሌላኛው ራሴን እንደ ፀሐፊ እመለከታለሁ እና በማስተላለፋቸው ፅሁፎች መልዕክቶች እና ሀሳቦች የማህበረሰቡን የባህልን እንዲሁም ሀይማኖት ላይ የማያቸውን አሉታዊ የጥላቻ አስተሳሰብ በመቃወም በፅሁፎቼ እቃወማለሁ የድርሻዬን በሚለው😊

**Emi Golden Habesha**
tnx ለጥያቄው💜 😎*/

ማናችንም የማንንም መብት በማይነካ መልኩ መብቶቻችን ማስከበር እንችላለን #በሀላል ከሚታይ ነገር #የተደበቀ ማንነት #የተደበቀ ሀላፊነቶች የተደበቁ ማንነቶች አሪፍ ናቸው ብዬ አስባለው🤔

**

# ክብሬ ኣቡካብ የተወሰዱ፡ በትጊሹ
# የሚመስላቹሁ

**Gloria Victor**

Gloria VictorWriting is my biggest way to speak out, under the name Gloria Victor I fight against rejection, hate, and society. Also, those small talks where I defend us when hate speech comes from others..And also, finding people who are allies to my beautiful community.

መፃፍ ከምቃወምባቸዉ መንገዶቹ ዋናዉ ነዉ። ግሎሪያ ቪክቶር በሚለዉ ስም ብዙ ተቃዉሞ፣ ጥላቻን እና ማህበረሰቡን እቃወማለሁ። የጥላቻ ንግግሮች በሚያጋጥሙኝ ሁኔታዎች ዉስጥ ለመብታችን እከራከራለሁ። የዉብ ማህበረሰባችን ደጋፊዎችን ሳገኝም እንደስኬት እቆጥረዋለሁ።

– GLORIA VICTOR

**ላያስችል አይሰጥም**

እንድሆን የምፈልገውና እንድሆን የተፈቀደልኝን ነገር ለይቼ አውቃለሁ። ስለዚህ የምፈልገው ሁሉ መብቴ አይደለም። ነገር ግን ሌሎችን ሳልጫን ፍላጎቴን አሟልቼ በጥንቃቄ መኖር እንደምችል አምናለሁ። ራሴን አደጋ ላይ የሚጥሉ ማስረጃዎችንና ሁኔታዎችን ላለማስቀረት እጥራለሁ። ማንም ያለ መረጃ እንዲከሰኝ አልፈቅድለትም፥ በማንኛውም ቦታ ከግብግብ ይልቅ ብልሃትና ትህትናን እመርጣለሁ። የተሻለ ነገ እስኪመጣ መብቴን ራሴን በማክበሬ ዉስጥ አገኘዋለሁ።

# ው ቢሆን ለመብታችሁ የቆማችሁ እንዴት ነው?